በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT AND CONSTRUCTION

# የተሻሻለ ኮንስትራክሽን ብቃት ማረጋገጫ ምዝገባ መመሪያ ቁጥር648/2013 ዓ.ም

# አጭር ማብራሪያ

ታህሳስ, 2013 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## 1. መግቢያ

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የተለያዩ ሀብቶችን ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት አስፈላጊ ወደሆኑ የግንባታ ወጤቶች የሚለወጥ እና እሴት የሚፈጥር ግዙፍ የኢኮኖሚ ዘርፍ ነው፡፡ በኢንዱስትሪው የስራ ተቋራጮች፣ የአማካሪ ድርጅቶች እንዲሁም በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች ምዝገባና ብቃት ማረጋገጫ አሰራር ስርዓት በየጊዜው በሚፈለገዉ መልኩ እየተሻሻለ አለመሄድ፣ የአሰራር ስርዓቱ ብቃታቸው በምዝና የተረጋገጡ ባለሙያዎችን የሚያበረታታ አለመሆን፣ በዕድሳት ወቅት እንደማስፈርት የሚጠየቀው የባለሙያዎችን የሙያ ብቃት ቀጣይነት እንዲረጋገጥ ማድረግ ኢንዱስትሪዉን ወደ ዘመናዊ አሰራር እንዲሸጋገር በማድረግ ተወዳዳሪነትን የሚያጎለብት አይነተኛ ሚና አለው፡፡ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው መንግስታዊ፣ የግል ድርጅቶችና ግለሰቦችን በባለቤትነት፣ በተቆጣጣሪነት፣ በአማካሪነት፣ በሥራ ተቋራጭነት፣ በግንባታ ዕቃዎች አምራችነት፣ በምህንድስና ዕቃዎች አዘጋጅነት፣ መሣሪያዎችና ፋይናንስ አቅራቢነት እና በግብይት ሥራ ላይ የተሰማሩ ባለሚናዎች በሙሉ የሚሳተፉበት ዘርፍ እንደ መሆኑ የብቃት ማረጋገጫ ምዝገባና ስርዓቱን በማስለጥና ስነምግባር የተላበሰ በማድረግ፤ ለጀማሪ ምሩቃን የስራ እድል ፈጠራን የሚያበረታታ በማድረግ፤ ከወጪው አለም የአማዛጋገብ ስርአት ጋር የተቀራረበና ለኢንዱስትሪው ዕድገትና ተወዳዳሪነት አስተዋጽኦ ሊያደርግ በሚችል ስረዓት ማንባት በወሳኝ መልኩ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ነው፡፡ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የኢኮኖሚና የማህበራዊ መሠረተ-ልማት አወታሮችን እንዲሁም ፋብሪካዎችና መኖሪያ ቤቶችን በማስፋፋት፣ የሥራ ዕድል በመፍጠር እና ሌሎች ዘርፎች እንዲስፋፉና እንዲለሙ በማድረግ የአገሪቱን ኢኮኖሚ የሚያሳድግ በመሆኑም ኢንደስትሪዉን ለሸከም የሚችል የኮንስትራክሽን ባለሞያ፣ድርጅት እና አማካሪዎችን እንዲፈጠር የኮንስትራክሽን ባለሙያዎች፣ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ብቃት ማረጋገጫ ምዝገባ ስረዓት እንዲዘረጋ ተደርጓል፡፡

## 2. የመመሪያው አስፈላጊነት፤ -

ሀ) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ተወዳዳሪ እንዲሆን ለማስቻል የኮንስትራክሽን ባለሙያዎች፣ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ብቃት ማረጋገጫ ምዝገባ ስረዓት የሚመራባቸው ህጎች ይሄወም የኮንስትራክሽን ስራ ተቋራጮችና ባለሙያዎች ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 19/2005 ዓ.ም እና የዲዛይን ባለሙያዎችና አማካሪዎች ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 22/2005ዓ.ም ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ፤

ለ) በኢንዱስትሪው የስራ ተቋራጮች፣ የአማካሪ ድርጅቶች እንዲሁም በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች ምዝገባና ብቃት ማረጋገጫ አሰራር ስርዓት በየጊዜው በሚፈለገዉ መልኩ እንዲሻሻል

ሐ) የአሰራር ስርዓቱ ብቃታቸው በምዝና የተረጋገጡ ባለሙያዎችን የሚያበረታታ እንዲሆን ለማስቻል

መ) በዕድሳት ወቅት እንደማስፈርት የሚጠየቀው የባለሙያዎችን የሙያ ብቃት ቀጣይነት እንዲረጋገጥ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ማኘቱ፤

ሠ) የኮንስትራክሽን ድርጅቶችን በተሰማሩባቸው ዘርፎች ባላቸው ልምድ ላይ ሳይሆን ማሽነሪዎች እና የቢሮ ቁሳቁሶች ላይ ያተኮረ ብቻ መሆኑን ማስቀረት

ረ) የብቃት ማረጋገጥና የምዝገባ ስዓርቱ በኢንዱስትሪው የሚታዩ ችግሮችን በመቅረፍ እሴት በሚጨምር እንዲሆን፤

ሰ) የብቃት ማረጋገጫ የምዝገባ ስርዓቱ ስነምግባር የተላበሰ በማድረግ፤ ለጀማሪ ምሩቃን የስራ እድል ፈጠራን የሚያበረታታ ለማድረግ፤

ሸ) የአማዘጋገብ ስርአቱ አለም አቀፍ ጋር የተቀራረበና ለኢንዱስትሪው ዕድገትና ተወዳዳሪነት አስተዋጽኦ ሊያደርግ በሚችል መልኩ እንዲፈጸም ለማስቻል የምዝገባና ብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶችን በአዲስ መልክ ማዘጋጀት በማስፈለጉ

ቀ) የኮንስትራክሽን ባለሙያዎችና ድርጅቶች በተሰጣቸው የምዝገባና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስረት እየሰሩ መሆኑን እያረጋገጠና የስነምግባር ችግርና የአፈጻጸም ክፍተት ያለባቸውን ለሚም እንዲቻል ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## 3. <u>የመመሪያው አላማ –</u>

የመመሪያው ዓላማ የአገሪቱ የኮንስትራሽን ኢንዱስትሪ ዘመናዊና ተወዳዳሪ እንዲሆን የኮንስትራክሽን ባለሙያዎችና ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትና የምዝገባ ስረዓት እንዲጠናከር በማድረግ ለላቀ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ላይ እንዲውል ማስቻል፡

## 4. <u>የመመሪያው ዝግጅት ሂደት</u>

የመመሪያው ዝግጅትና ማሻ በአንድ በኩል በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የኮንስትራክሽን ባለሙያዎችና ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትና የምዝገባ ስርዓት አሁን ያለውን የኢንዱስትሪውን አቅም ለሸከም የሚችል እንዲሆን እሳቤ በመኖሩ በሌላ በኩል በተገልጋዩ የሚነሱ ቅሬታዎች በመኖሩ ምክንያት ችግሩን በዘለቄታዊ ለመፍታት እንዲቻል መጀመሪያ የመረጃ ማሰባሰቢያ ቅጽ ተዘጋጅቶ ከባለድሻ አካላት መረጃ ማሰባሰብ ስራ ተከናወናዋል በመቀጠልም የተሰበሰበውን መረጃ በመተንተን ለመመሪያው ግብአት እንዲሆን የተደረገ ሲሆን በመመሪያ ዝግጅቱም ረቂቅ ሂደት ላይ ባለድርሻ አካላት ሰፊ ሚና እንዲኖራቸው ተደርጓል በረቂቅ ሂደቱም በስራ ክፍል፣በቢሮ፣በዘርፍ ሜኔጅመንት፣ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሜኔጅመንት፣ከክልሎች እና ባለድርሻ አካላት ጋር መድረክ በመፍጠር፣ በሚኒስቴር ማሰሪያ ቤቱ ዌብ ሳይት ላይ ተጭኖ ሰፊ አስተያየት እንዲሰጥበት በማድረግ ጠቃሚ ሃሳቦችም እንዲካተቱ ተደርገዋል

በሚጨሻ በድጋሚ በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሜጅመንት አባላት ቀርቦ የጋራ መግባባት ላይ ከደረሰ በኋላ እንዲማዘገብ ለጠቅላይ አቃቢ ህግ እንዲላክ ወሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## 5. የረቂቅ መመሪያው ይዘት

### ክፍል አንድ

በክፍል አንድ ስር ጠቅላላ ድንጋጌን በዋና ርዕስነት ይዞ በሶስት አንቀፆች የተዋቀረ ሲሆን እነርሱም አጭር ርዕስ፣ትርጓሜ የተፈፃሚነት ወሰን በሚያዝ የተዋቀረ ነው፡፡ ይህ ክፍል ለመመሪያው አጠቃላይ ከመመሪያ ስያሜ የቃላት ትርጓሜ እንዲሁም መመሪያው በማን ላይ እስከምን ድረስ ነው ተፈፃሚ የሚሆነው የሚሉዋን ጉዳይ በግልፅ ደንግጎ የሚያልፍ የመመሪያው የመጀመሪያ ክፍል ነው፡፡

**ጠቅላላ ድንጋጌ፡ -**

**አንቀጽ አንድ**

በዚህ ክፍል ወስጥ አንቀጽ አንድ የአዋጁን ስያሜ የያዘ ሲሆን ስያሜውም የተሻሻለ የኮንስትራክሽን ባለሞያዎች፣ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች የብቃት ማረጋገጫ የምዝገባ መመሪያ ቁጥር......../2013ዓ.ም መሆኑ ተመላክቷል

**በአንቀጽ ሁለት**

ትርጓሜ ላይ በአዋጁ ተደጋግመው ጥቅም ላይ የዋሉና አዋጁን ለሚዳትና ለመተገበር ትርጉም ያስፈልጋቸዋል ተብለው የታመነባቸውን ቃላት ትርጉም ለማስጠት ተሞክሯል፡፡ በዚህ ሂደት ለመመሪያው ተፈላጊ ቃላት ሆነው ከዚህ በፊት በወጡ ህጎች የዚህን መመሪያ ፍላጎት በሚያሟላ ሁኔታ ትርጉም የተሰጣቸውን ለምሳሌ፡ - ክልል፣ድርጅት፣ኮንስትራክሽን...... ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉ ቃላት ትርጉማቸው በቀጥታ ከነባሮቹ ህጎች እንዲወሰድ ተደርጓል፡፡ በዚህ መመሪያ በአዲስነት ጥቅም ላይ የዋሉ ወይንም ከሌሎች ነባር ህጎች የተለየ እንድምታ በያዘ ትርጉም ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላት ለምሳሌ፡ - ሞያተኛ፣ ልዩ አማካሪ፣ልዩ ስራ ተቋራጭ......ወ.ዘ.ተ በዚህ መመሪያ አጠቃቀማቸውን ማስረት ያደረገ ትርጉም ተሰጥቷቸዋል፡፡

**በአንቀፅ ሶስት፡**

የተፈፃሚነት ወሰን የሚያመላከት ሲሆን መመሪያው በኮንስትራክሽን ስራዎች እና አገልግሎቶች ላይ በሚሰማሩ የኮንስትራክሽን ባለሞያዎች ድርጅቶች፤እና ፕሮጀክቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ በመመሪያው መግቢያ ላይ እንደተመላከተው የኮንስትራክሽን ዘርፍ በባህሪው የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ ስለሆነ ተፈጻሚነቱም እነማን ላይ እንደሚሆን ተመልክቷል፡፡

### ክፍል ሁለት

በዚህ ክፍል የኮንስትራክሽን ባለሙያ፣ ድርጅት እና ፕሮጀክት ምዝገባና ብቃት ማረጋገጫ ስነ-ሥርዓት የሚደነግግ ሆኖ ስለ ምዝገባ፤ማመልከቻን ወድቅ ስለማድረግ፣ የምዝገባ እና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማስጠት፣የምዝገባ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመመለስ፣ስለ ምዝገባ እና ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ዕድሳት፣ስለ ምዝገባ እና ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ደረጃ እድገት፣የባለሙያ ምዝገባ ወይም የድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማገድ፣የባለሙያ ፈቃድ ወይም የድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማሰረዝ፣ምትክ የባለሙያ ምዝገባ እና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማስጠት፣ስለ ውክልና፣ስለ ክትትልና ቁጥጥር በማከታተል የያዘ ሲሆን በስሩ በአስራ ሁለት አንቀፆች ተብራርቷል፡፡

**አንቀፅ አራት**

ይህ አንቀፅ አጠቃላይ ማንኛውም የሀገር ወስጥ ወይም የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው የኮንስትራክሽን ባለሙያ፣ድርጅትና ፕረጀክቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ወይም ምዝገባ መመዝገብ፤ማሻሻል፣ማደስ እንዲሁም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትና የምዝገባ የሚይዛቸው ነጥቦች የሚደነግግ ነው

**አንቀፅ አምስት**

በዚህ አንቀፅ ስር የተደነገገው የኮንስትራክሽን ባለሙያ፣ድርጅትና ፕረጀክቶች የብቃት ማረጋገጫ ወይም ምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማገኘት የሚቀርቡት ማመልከቻ ወድቅ የሚደረግባቸው የህግ ምክንያቶች የተዘረዘሩበት ድንጋጌ ነው፡፡

**አንቀፅ ስድስት**

ይህ አንቀፅ አመልካችቶች በመሙያው የተቀመጡትን መስፈርቶች አሟልቶ ሲቀርብ ብቻ በህግ የተቀመጠውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል የብቃት ማረጋገጫ ወይም ምዝገባ ምስክር ወረቀት ማስጠት እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡

**አንቀፅ ሰባት**

በዚህ አንቀፅ ስር የኮንስትራክሽን ባለሙያ፣ድርጅትና ፕረጀክቶች የወሰደውን የብቃት ማረጋገጫ የምዝገባ ምስክር ወረቀት የሚመለስባቸው ምክንያቶች በዝርዝር የተቀመጠበትና አስገዳጅ አንቀፅ ነው

**አንቀፅ ስምንት**

በዚህ አንቀፅ ስር የተደነገገው የብቃት ማረጋገጫ የምዝገባ ምስክር ወረቀት የወሰዱ የኮንስትራክሽን ባለሙያ፣ድርጅትና ፕረጀክቶች የምስክር ወረቀቱን መቼ እድሳት እንደሚያደርጉ፣የእድሳት ጊዜ ያለፈባቸው በቅጣት እንደ ሚያሳድሱና ለባለሙያና ለድርጅቶች የስራ ላይ ስልጠና ለማደስ እንደ መስፈርት ማጠቀም እንደሚቻል ይደነግጋል፡፡

**አንቀፅ ዘጠኝ**

ይህ አንቀፅ የሚደነግገው የኮንስትራክሽን ባለሙያ፣ድርጅትና ፕረጀክቶች ቀድሞ የወሰዱትን የብቃት ማረጋገጫ የምዝገባ ምስክር ወረቀት በመሚያው የተቀማጠወን ማስፈርቶች ከማሟላት በተጨማሪ የብቃት ምዝና በማቅረብ ደረጃ እደገት ማድረግ እንደሚችል መሆኑ በግልፅ ተመላክቷል፡፡

**<u>አንቀፅ አስር</u>**

በዚህ አንቀፅ ስር በመሚያው መሠረት ለኮንስትራክሽን ባለሙያና ድርጅት የተሰጡ የብቃት ማረጋገጫ የምዝገባ ምስክር ወረቀት የሚታገዱበት የህግ ምክንያቶች በዝርዝር የሚደነግግ አንቀፅ ነው፡

**<u>አንቀፅ አስራ አንድ</u>**

በዚህ አንቀፅ ስር በመሚያው መሠረት ለኮንስትራክሽን ባለሙያና ድርጅቶች የተሰጡ የብቃት ማረጋገጫ የምዝገባ ምስክር ወረቀት የሚሰረዝበት የህግ ምክንያቶች በዝርዝር የሚደነግግ አንቀፅ ነው፡

**<u>አንቀፅ አስራ ሁለት</u>**

ይህ አንቀፅ የሚደነግገው ለኮንስትራክሽን ባለሙያና ድርጅቶች ምትክ የብቃት ማረጋገጫ የምዝገባ ምስክር ወረቀት የሚሰጥበት የህግ አግባብ የሚደነግግ አንቀፅ ነው፡

**<u>አንቀፅ አስራ ሶስት</u>**

ይህ አንቀፅ የሚደነግገው በውክልና ስለ ማስተናገድ ሲሆን ማንኛውም የኮንስትራክሽን ባለሙያ ወይም ድርጅቶች አዲስ ወይም ለእድሳት ወይም ለደረጃ እድገት የብቃት ማረጋገጫ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማግኘት በአካል በመቅረብ ወይም በህጋዊ ወኪል አማካኝነት አግልግሎት ማግኘት እንደሚቻል፣ሆኖም በውክልና ሁለት ተከታታይ ጊዜ ማስተናገድ እንደማይቻል በግልፅ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

**<u>አንቀፅ አስራ አራት</u>**

በዚህ አንቀፅ የብቃት ማረጋገጫ የምዝገባ ምስክር ወረቀት የሰጠው አካል ባለሞያው ወይም ድርጅቱ በተሰጠው ምስክር ወረቀት በህግ አግባብ እየተገለገለበት ነው ወይ ከአላማው ዉጪ አገልግሎት እየሰጠም ከሆነ እርምጃ ለመውሰድ ለአገልግሎት ሰጪአካል የክትትልና ቁጥጥር ስልጣን የሚሰጥ አንቀፅ ነው፡

**<u>ክፍል ሶስት</u>**

በክፍል ሶስት ስር በዋናነት የኮንስትራክሽን ባለሞያዎች፣ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ምድብ የሚደነግግ ሆኖ በስሩ አራት አንቀፆችን የያዘ ሲሆን እነርሱም የባለሞያዎችና የሞያተኞች ምድብ፣ የስራ ተቋራጭ ምድብ፣ የአማካሪዎች ምድብ እና የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ምድብ በሚል ራሳቸው በቻሉ አንቀፆች ተዋቅሮ ይገኛል፡፡

**<u>አንቀፅ አስራ አምስት</u>**

ይህ አንቀፅ የባለሞያዎችና የሞያተኞች እንደ ሞያ አይነታቸው ምድብ ተሠጥቷቸው የሚገኙ ሲሆን በተጨማሪም አዲሱ የትምህርት ስረዓት መሠረት ተደርጎ የብቃት ማረጋገጫ ምዝና እንደ አንድ ወሳኝ እንደ አንድ ማስፈርት ተወስዶ በማያሻማ ሁኔታ በግልፅ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

**አንቀፅ አስራ ስድስት**

ይህ አንቀፅ የስራ ተቋራጭ ምድብ እንደየ ስራ ምርጫቸው በዋናነት አራት አይነት የስራ ተቋራጮች የተቀመጡ ሲሆን በአራተኛው አይነት ማለትም በልዩ የስራ ተቋራጭ ስር ዘርዘር ያሉ ለአፈፃፀም በሚያመቹ ሁኔታ ብዙ የሞያ አይነቶች ተደንግጎ የሚገኝበት አንቀፅ ነው፡፡

**አንቀፅ አስራ ሰባት**

ይህ አንቀፅ የአማካሪዎች ምድብ እንደየ ስራ ምርጫቸው በዋናነት አምስት አይነት የአማካሪ አይነቶች የተቀመጡ ሲሆን በአምስተኛው አይነት ማለትም በልዩ አማካሪ ስር ዘርዘር ያሉ ለአፈፃፀም በሚያመቹ ሁኔታ ብዙ የሞያ ማስኮች ማማከር አይነቶች ተደንግጎ የሚገኝበት አንቀፅ ነው፡፡

**አንቀፅ አስራ ስምንት**

በዚህ አንቀፅ ስር በመመዪያው መሠረት ማስፈርቱን አሟልተው የሚመዘገቡ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ምድብ እንዲኖራቸው የተደነገገ ሲሆን ምድቦቹም አነስተኛ ህንፃ፣መካከለኛ ህንፃ፣ከፍተኛ ህንፃና በጣም ከፍተኛ ህንፃ በሚል ፕሮጀክቶች ተመድበው የሚገኙበት አንቀፅ ነው፡፡

**ክፍል አራት**

በዚህ ክፍል ስር የኮንስትራክሽን ባለሞያዎችና ሞያተኞች የብቃት ማረጋገጫ የምዝገባ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ስነ-ስረዓት የተደነገገበት ሲሆን በአጠቃለል በስሩ በአምስት አንቀፆች ይዞ በዋናናነት አመልካቾች አሟልተው መቅረብ የሚገባቸው ነገሮች፣የአሰጣጥ አፈፃፀም እንዲሁም የሞያተኛ አይነቶችን በማዘርዘር ግልፅ በሆነ የህግ አግባብ አካታች ሆኖ የተብራራበት ክፍል ነው፡፡

**አንቀፅ አስራ ዘጠኝ**

በዚህ አንቀፅ ስር ኢትዮጰያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጰያዊ ወይም የውጪ ሀገር ዜግነት ያላቸው የኮንስትራክሽን ባለሞያዎችና ሞያተኞች የብቃት ማረጋገጫ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለመውሰድ ሲያመለክቱ አሟልተው ሊቀርቡ የሚገባቸው ዝርዝር ነጥቦችን ይዞ የተደነገገ አንቀፅ ነው፡፡

**አንቀፅ ሀያ**

ይህ አንቀፅ የሚደነግገው የኮንስትራክሽን ባለሞያዎችና ሞያተኞች የብቃት ማረጋገጫ የምዝገባ የሚያመለከታቸው ባለሞያዎች ለይቶ የሚያስቀምጥ ሲሆን የምስክር ወረቀቱ አሰጣጥና አፈፃፀም ለቀርቡ የሚገባቸው ነጥቦችን አካቶ የያዘ አንቀፅ ነው፡፡

**አንቀፅ ሀያ አንድ**

ይህ አንቀፅ የሚዳነግገው ስለ አነስተኛ መካተኛ ብቃት ሚረጋገጫ ምዝገባ የሚያካትታቸው የትኛወን የሙያ ደረጃ እንደሆነና ለአገልግሎት ሲቀርቡ ሊያሟሏቸው የሚገቡ ነጥቦች ጭምር ይዞ በግልፅ የሚዳነግግ አንቀፅ ነው፡፡

**አንቀፅ ሀያ ሁለት**

ይህ አንቀፅ የሚዳነግገው ስለ ማስተኛ መካተኛ ብቃት ሚረጋገጫ ምዝገባ የሚያካትታቸው የትኛወን የሙያ ደረጃ እንደሆነና ለአገልግሎት ሲቀርቡ ሊያሟሏቸው የሚገቡ ነጥቦች ጭምር ይዞ በግልፅ የሚዳነግግ አንቀፅ ነው፡፡

**አንቀፅ ሀያ ሶስት**

ይህ አንቀፅ የሚዳነግገው ስለ ከፍተኛ ባለሞያ ብቃት ሚረጋገጫ ምዝገባ የሚያካትታቸው የትኛወን የሙያ ደረጃ እንደሆነና ለአገልግሎት ሲቀርቡ ሊያሟሏቸው የሚገቡ ነጥቦች ጭምር ይዞ በግልፅ የሚዳነግግ አንቀፅ ነው፡፡

**ክፍል አምስት**

በዚህ ክፍል ስር የኮንስትራክሽን ስራ ተቋራጭ የብቃት ሚረጋገጫ የምዝገባ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ስነ-ስረዓት የተደነገገበት ሲሆን በአጠቃላል በስሩ በአራት አንቀፆች ይዞ በዋናናነት አመልካቾች አሟልተው መቅረብ የሚገባቸው ነገሮች፣የአሰጣጥ አፈፃፀም እንዲሁም የተቋራጮች ደረጃ፣የፕረጀክት ማጠን፣የመሳሪያና የሰው ሀይል ማስፈርት፣ መጫረቻ ዋጋ ማጠን እንዲሁም በልዩ ሁኔታ ማስተናገድ የሚቻልበት ሁኔታ ግልፅ የተብራራበት ክፍል ነው፡፡

**አንቀፅ ሀያ አራት**

በዚህ አንቀፅ ስር ኢትዮጰያዊ ወይም ትወልደ ኢትዮጰያዊ ወይም የወጪ ሀገር ዜግነት ያላቸው የኮንስትራክሽን ስራ ተቋራጭ የብቃት ሚረጋገጫ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለመውሰድ ሲያመለክቱ አሟልተው ሊቀርቡ የሚገባቸው ዝርዝር ነጥቦችን ይዞ የተደነገገ አንቀፅ ነው፡፡

**አንቀፅ ሀያ አምስት**

በዚህ አንቀፅ ስር የተቋራጮች ደረጃ፣የፕሮጀክት ማጠን፣የመሳሪያና የሰው ሀይል ማስፈርት በተመለከተ በዝርዝር ለአፈፃፀም በሚያመች መልኩ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በዋናነት አመልካቾች በመመዪያው መሠረት ከተቀመጡት ደረጃዎች ወስጥ በአንዱ የብቃት ሚረጋገጫ ወይም ምዝገባ ሚድረግ የሚችሉ መሆኑን ጭምር ተደንግጎ ይገኛል፡፡

**አንቀፅ ሀያ ስድስት**

ይህ አንቀፅ የሚዳነግገው ስለ ተቋራጮች ከፍተኛ የመጫረቻ ዋጋ ማጠን ሲሆን የመጫረቻ ዋጋወም የመመዪያው አካል በሆነው ከሰንጠረዥ 6 እስከ 8 ማሰረት እንደሚሆን የተደነገገበት አንቀፅ ነው፡፡

**<u>አንቀፅ ሀያ ሰባት</u>**

በዚህ አንቀፅ ስር በልዩ ሁኔታ ተቋራጮች ሆነው ለማስራት ማስፈርቱን አሟልተው በኮንስትራክሽን ስራ ላይ በቂ የስራ ልምድ ያላቸው በልዩ ሁኔታ የቅድሚያ ማስፈርት ሳያስፈልጋቸው የሚስተናገዱበት እዚሁ ላይ ሴቶች ባለሞያዎች እና አካል ጉዳተኞች የሚጠየቀው አገልግሎት በልዩ ሁኔታ ዝቅ እንዲል የሚያስችል ድንጋጌ ነው፡፡

**<u>ክፍል ስድስት</u>**

በዚህ ክፍል ስር የአማካሪ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ የምዝገባ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ስነ-ስረዓት የተደነገገበት ሲሆን በአጠቃለል በስሩ በአራት አንቀፆች ይዞ በዋናናነት አመልካቾች አሟልተው መቅረብ የሚገባቸው ነገሮች፣የአሰጣጥ አፈፃፀም እንዲሁም የአማካሪዎች ደረጃ፣የፕረጀክት ማጠን፣የመሳሪያና የሰው ሀይል ማስፈርት፣ መጫረቻ ዋጋ ማጠን እንዲሁም በልዩ ሁኔታ ማስተናገድ የሚቻልበት ሁኔታ ግልፅ የተብራራበት ክፍል ነው፡፡

**<u>አንቀፅ ሀያ ስምንት</u>**

በዚህ አንቀፅ ስር ኢትዮጵያዊ ወይም ትወልደ ኢትዮጵያዊ ወይም የውጪ ሀገር ዜግነት ያላቸው የአማካሪ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለመውሰድ ሲያማለክቱ አሟልተው ሊቀርቡ የሚገባቸው ዝርዝር ነጥቦችን ይዞ የተደነገገ አንቀፅ ነው፡፡

**<u>አንቀፅ ሀያ ዘጠኝ</u>**

በዚህ አንቀፅ ስር የአማካሪዎች ደረጃ፣የፕሮጀክት ማጠነ ረ፣የመሳሪያና የሰው ሀይል ማስፈርት በተማለከተ በዝርዝር ለአፈፃፀም በሚያመች ሜልኩ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በዋናነት አመልካቾች በመሚያው መሠረት ከተቀማጡት ደረጃዎች ወስጥ በአንዱ ወይም ከአንድ በላይ የብቃት ማረጋገጫ ወይም ምዝገባ ማመልከት የሚቹሉ መሆኑን ጭምር ተደንግጎ ይገኛል፡፡

**<u>አንቀፅ ሰላሳ</u>**

ይህ አንቀፅ የሚደነግገው ስለ አማካሪዎች ከፍተኛ የፕሮጀክት ዋጋ ማጠን ሲሆን ከፍተኛው የፕሮጀክት ዋጋ ማጠን የመሚያው አካል በሆነው ከሰንጠረዥ 14 እስከ 15 ማሰረት እንደሚሆን የተደነገገበት አንቀፅ ነው፡፡

**<u>አንቀፅ ሰላሳ አንድ</u>**

በዚህ አንቀፅ ስር በልዩ ሁኔታ አማካሪዎች ሆነው ለማስራት ማስፈርቱን አሟልተው በኮንስትራክሽን የማማከር ስራ ላይ በቂ የስራ ልምድ ያላቸው የዩኒቨርስቲ መምህራን አማካሪ ለመሆን ፍላጎት ያላቸው በልዩ ሁኔታ የቅድሚያ ማስፈርት ሳያስፈልጋቸው የሚስተናገዱበት እንዲሁም ሴቶች ባለሞያዎች እና አካል ጉዳተኞች የሚጠየቀው አገልግሎት በልዩ ሁኔታ ዝቅ እንዲል የሚያስችል ድንጋጌ ነው፡፡

**<u>ክፍል ሰባት</u>**

በዚህ ክፍል ስር የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ምዝገባ ስነ-ስረዓት፣የማዝጋቢ አካል ኃላፊነት እና የተማዝጋቢ አካል ኃላፊነት የተደነገገበት ሲሆን በአጠቃላል በስሩ ሶስት አንቀፆች ግልፅ የተብራራበት ክፍል ነው፡፡

**አንቀፅ ሰላሳ ሀለት**

በዚህ አንቀፅ ስር ማኛወም የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች በዚህ መመሪያ መመዝገብ ግዴታ እንደሆነና ለማዝገብ የሚመጣ ፕሮጀክት ሊያሟቸው የሚገቡ ነገሮችን ዘርዝሮ የሚደነግግ አንቀፅ ነው፡፡

**አንቀፅ ሰላሳ ሶስት**

በዚህ አንቀፅ ስር በመመሪያው መሠረት የኮንስትራክሽን ባለሞያዎች፣ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች የብቃት ሚረጋገጫ የማስጠትና የመመዝገብ ስልጣን የተሰጠው አካል ያለበትን ኃላፊነት እና ግዴታ የሚደነግግበት አንቀፅ ነው፡፡

**አንቀፅ ሰላሳ አራት**

በዚህ አንቀፅ ስር በመመሪያው መሠረት በኮንስትራክሽን ባለሞያዎች፣ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች የብቃት ሚረጋገጫ ለማግኘትና ለመመዝገብ የሚቀማከት ማኛወም ተማዝጋቢ አካል ያለበት ኃላፊነት እና ግዴታ በግልፅ የሚደነግግ አንቀፅ ነው፡፡

**ክፍል ስምንት**

በዚህ ክፍል ስር በመመሪያው ዋና ክፍል ወስጥ ያልተካከቱ አጠቃላይ ለመመሪያው አፈፃፀም ትልቅ ድርሻ ያለው ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን በአጠቃላል በስሩ ዘጠኝ አንቀፆች ይዞ የተብራራበት ክፍል ነው፡፡

**አንቀፅ ሰላሳ አምስት**

በዚህ አንቀፅ ስር ማኛወም ተገልጋይ ወይም ተማዝጋቢ አካል በአገልግሎት አሰጣጡ ሆነ በተወሰዱ ወሳኔዎችና እርምጃዎች ላይ ቅሬታ ሲያጋጥመው ቅሬታ ማቅረብ መብት እንደሆነ የሚደነግግ አንቀፅ ነው፡፡

**አንቀፅ ሰላሳ ስደስት**

ይህ አንቀፅ የሚደነግገው ስለ ተጠያቂነት ሲሆን በስሩ ማዝጋቢም ሆነ ተማዝጋቢ አካል ከዚህ መመሪያ ወጪ አገልግሎት የሰጡ ወይም ያገኙ እንደሆነ አገልግሎቱ ማስረዝ ወይም የወሳኔው ማስተካከል እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ባለው ህግ እንደሚጠየቁ የተደነገገበት አንቀፅ ነው፡፡

**አንቀፅ ሰላሳ ሰባት**

ይህ አንቀፅ የሚደነግገው ማዝጋቢ አካል ወይም ምስክር ወረቀት ሰጪ አካል ባወጣው ህግ ማስረት አገልግሎት ለሰጠበት የሚያስከፍለው ክፍያ የተደነገገበት አንቀፅ ነው፡፡

**አንቀፅ ሰላሳ ስምንት**

ይህ አንቀፅ የሚደነግገው ማኛወም አካል ይህንን መመሪያ በሥራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ ያለበት መሆኑን የጠደነገገበት አንቀፅ ነው፡፡

**አንቀፅ ሰላሳ ዘጠኝ**

በዚህ አንቀፅ ስር የባለሙያና የማሪያዎች የመተካካት አሰራር በተማከተ በሚ/ር መ/ቤቱ የበላይ አሚራር እንደ የአስፈላጊነቱ ቀርቦ የወስጥ አሰራር መወሰን እንደሚችል ለሚኒስቴር ማሪያቤቱ ኃላፊነት የሰጠ አንቀፅ ነው፡፡

**አንቀፅ አርባ**

ይህ አንቀፅ የሚደነግገው የማሸጋገሪ ሀሳብን ሲሆን ይሄውም መመሪያው ሥራ ላይ ከሚውልበት ቀን በፊት የነበሩ አሰራሮች በአዲሱ አሰራር ሙሉ ለሙ ወደ ስራ እስኪገባ ቀደሞ የነበረው አሰራር ጊዜ ተቀምጦለት የሚስተናገደበት የህግ አግባብ ነው ይሄ ደግሞ የተስተካከለ የሽግግር ሁኔታን የሚፈጥር ነው፡፡

**አንቀፅ አርባ አንድ**

ይህ አንቀፅ የሚደነግገው የጠሸሩ ህጎችና ዘልማዳዊ አሰራሮች ሲሆን ከዚህ ቀደም በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር መ/ቤት ወጥቶ የነበረው የኮንስትራክሽን ባለሙያዎችና ስራ ተቋራጮች ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 19/2005 ዓ.ም እንዲሁም የዲዛይን ባለሙያዎችና አማክሪዎች ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 22/2005 ዓ.ም በዚህ መመሪያ የተሸሩ መሆኑን የተደነገገበት አንቀፅ ነው፡፡

**አንቀፅ አርባ ሁለት**

ይህ አንቀፅ የሚደነግገው መመሪያወን ስለ ማሻሻል ሲሆን በዚህም የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር አሰፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ይህን መመሪያ ሊያሻሽል እንደሚችል በአንቀፁ ተደንግጎ ይገኛል

**አንቀፅ አርባ ሶስት**

ይህ አንቀፅ የሚደነግገው መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ ሲሆን በዚህም መመሪያው ፀድቆ ወደ ተግባር ሲገባ ተፈፃሚ እንደሚሆን የተደነገገበት አንቀፅ ነው፡፡

## 6. ማጠቃለያ

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 1097/2011 በአዲስ መልክ ሲደራጅ ከተሰጡት ሥልጣንና ኃላፊነት አንዱ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተወዳዳሪነት ብቃት ያለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለማንባት የሚያስችሉ የተሟቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፤ በዲዛይን፣ በጨረታና፣ በኮንትራት ይዘት ላይ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበት ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል የሚል ሲሆን ከዚህ አኳያ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ማንግስታዊ፣ የግል ድርጅቶችና ግለሰቦችን በባለቤትነት፣ በተቆጣጣሪነት፣ በአማክሪነት፣ በሥራ ተቋራጭነት፣ በግንባታ ዕቃዎች አምራችነት፣ በምህንድስና ዕቃዎች አዘጋጅነት፣ መሣሪያዎችና ፋይናንስ አቅራቢነት እና በግብይት ሥራ ላይ የተሰሙ ባለሜዎች በሙሉ የሚስተፉበት ዘርፍ እንደ መሆኑ የብቃት ሚረጋገጫ ምዝገባና ስርዓቱን በማክለጥና ስነምግባር የተላበሰ በሚድረግ፤ ለጀሜ ምሩቃን የስራ እድል ፈጠራን የሚበረታታ በሚድረግ፤ ከወጪው አለም የአማዘጋገብ ስርአት ጋር

የተቀራረበና ለኢንዱስትሪው ዕድገትና ተወዳዳሪነት አስተዋጽኦ ሊያደርግ በሚችል ስረዓት ማንባት እና ጠንካራ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበት የተጠናከረ የአሰራር ሥርዓት በማዘርጋት ግልፀኝነትና ተጠያቂነት ማስፈን እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ ይህ መመሪያ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል በመሆኑም መመሪያው በቶሎ ፀድቆ ወደ ስራ የሚገባ ይሆናል፡፡